ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቓስ ህዝቢ ትግራይ (ዴ.ም.ህ.ት)
ትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ት.ህ.ዴ.ን)
Tigray People's Democratic Movement (T.P.D.M)

**በየመን መንግስትና በወያኔ ስርአት በግንቦት 7 ዋና ፀሃፊ ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተወሰደውን ያፈና ተግባር በመቃወም፣ ከትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተሰጠ ድርጅታዊ መግለጫ**

የወያኔ ኢህአዴግ ስርአት ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል እየፈፀመ መቆየቱና አሁንም እየቀጠለበት መሆኑ ይታወቃል። የወያኔ አምባገነን ስርአት ህዝቡን እየጨፈጨፈና ለነፃነት የቆሙትን ቁርጠኛ ታጋዮች በመግደል፣ የህዝቡን የትግል ማእበል መግታት እንደማይቻለው ካለፉት አባቶቹ መማር በተገባው ነበር።

ትናንት በወያኔዎች ቀጥተኛ መሪነት ይካሄድ በነበረው የትጥቅ ትግል በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖች ለጭቁኑ ህዝብ ሲሉ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ተዋግተው በከፈሉት መስዋእትነት ህዝባዊ ትግሉ በበለጠ እልህና ቆራጥነት ሲቀጥል እንጂ፣ በመስዋዕትነቱ ምሬት ተደናግጦና ተስፋ ቆርጦ ትግሉ ወደ ኋላ ሲመለስና ትርጉም የለሽ ሲሆን አልታየም። ምክንያቱም ትግል ሲባል ሁሉም አይነት መስዋእትነት ከፍለህ ከአፈናና ከጭቆና ነፃ በማውጣት ለህዝቡ ፍትህ፤ እኩልነትና ዴሞክራሲ ማስፈን ስለሆነ፡ ይህ በታጋይ እንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተፈጸመው የእገታ እርምጃ ትግሉን የበለጠ ያቀጣጥለዋል እንጂ ወያኔ እንደተመኘው ትግሉን አያዳክመውም። አንዳርጋቸው እንደ አንድ ታጋይ መሪ ለትግሉ የከፈለው መስዋዕትነትም ለዘአለም ህያው ሆኖ ይኖራል።

ስለሆነም የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴ.ን/ ይህ በየመን መንግስት በታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተፈፀመው ታሪካዊ ስህተት በሁሉም የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ላይ የተፈፀመ እንደሆነ በማመን እኩይ ተግባሩን በፅኑ ያወግዛል።

ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ ለህዝብ ብሎ የከፈለው መስዋእትነት አላማውን አምነው ለህዝብና ለሃገር ነጻነት ትግሉ የሚያስፈልገውን የህይወት መስዋእትነት ሁሉ ከፍለው አገራቸውን ነጻ ለማውጣት የቆረጡ እልፍ አእላፍ ጀግኖችን ይፈጥራል ብሎ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ትህዴን ያምናል። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ አንዳርጋቸው ፅጌና ሌሎች በሺህ የሚቆጠሩ ታጋዮች እስከዛሬ ዋጋ የከፈሉለትን ትግል ለድል ለማብቃትና የአምባገነኑ ስርአት እድሜ ለማሳጠር ዛሬውኑ ትግሉን እንዲቀላቀል በዚህ አጋጣሚ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴ.ን/ ጥሪውን ያቀርባል።

ዘለአለማዊ ታሪክ እንጂ ዘለአለማዊ ህይወት የለም!
የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ

ሓምሌ 2/2006 ዓ/ም
ድል ለጭቁኖች!!